የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)
Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

# *የወረርሺኝ (ኮሌራ) በሽታ የዜጎችን ሕይወት መቅጠፉን እንደቀጠለ ነው!!*

ጳጉሜ 4 ቀን 2001 ዓ.ም.

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ(ኢሕአፓ) የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የኢትዮጵያ ሕዝብ በኮሌራ በሽታ መጠቃቱን በወቅቱ አለማሳውቁ ብቻ ሳይሆን የሕክምና ባለሙያ ዶክተሮችና የጤና ጥበቃ ሠራተኞች ስለ ተከሰተው በሽታ አይነት በተለይም ኮሌራ መሆኑና አለመሆኑን አስመልክቶ ምንም አይነት ዜና እንዳያሰራጩ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ መስጠቱን አጥብቆ ያወግዛል።

ይህ የመለስ አገዛዝ በማን አልበኝነት "የተቅማጥ በሽታ" ነው በማለት በዜና ማሰራጫዎች በሀሰት ሲያሰራጭ የነበረው በሽታ የኮሌራ በሽታ መሆኑ የተረጋገጠ ከመሆኑም በላይ እያለ የገለጸው በሽታ ከመቶዎች በላይ የሚሆኑ ዜጎችን ሕይወት ማስገበሩ ታውቋል። የመለስ አገዛዝ ባለፉት 18 አመታት የሀገሪቱን የጤና ጥበቃ ሥርአት በባዕዳን ደጋፊዎቹ አማካኝነት "አመርቂና አበረታታች ውጤት" ተገኝቷል እያለ ቢያስለፈልፍም የጤና ተቋሙንና የተያያዙ የሥራ መስኮችን ለከፍተኛ ጉዳት የዳረጋቸው መሆኑ በገሃድ የሚታይ ብቻ ሳይሆን በመረጃ የተደገፍም ህዝብ የሚያውቀው ህቅ ነው። በዚህም የተነሳ ሕብረተሰቡ የሚፈልገውን አይነት የጤና አገልግሎት ሊያገኝ ባለመቻሉ በተለያዩ በሽታዎች እየተጠቃ ይገኛል። የዚህ ሁኔታ ዋነኛ ተጠቂዎች ደግሞ ሕጻናት፣ ወጣቶችና በወሊድ ወቅት የሚገኙ ሴቶች መሆናቸው የአደባባይ ሚስጢር ነው።

ይህ በመዲናችን ሳይቀር ተከስቶ በሚገኘው የውሃና የሃይል እጥረት በቋፍ ላይ ያለውን የጤና ዘርፍ ለከፋ ችግር በመዳረጉም የከተማዋ አይነተኛ ሁኔታ እየሆነ መምጣቱ ብቻ ሳይሆን ለተላላፊ በሽታዎች አመቺ ሁኔታ እየፈጠረ ይገኛል። በመዲናዋ እየታዩ ያሉት ዋና ዋና የጤና ችግሮች ቲቪ፣ ኤድስ፣ ከአኗኗር ከአመጋገብ ጋር ተያይዘው የሚመጡ በሽታዎችና ድንገተኛ አደጋዎች እንዲሁም በውሃ ወለድና በተለያዩ ምክንያቶች የሚከሰቱ አጣዳፊ ተቅማጥና ትውከት፣ የደም ግፊትና የስኳር በሽታዎች በአብነት የሚጠቀሱና በብዛትም የሚታዩ ናቸው።


PRP
O.Box 73337
ashington DC, 20056
SA
l. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

በነዚህ በሽታዎች የሚጠቃው የሕዝብ ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መሆኑን ደግሞ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በውጭ ሀገር በሚኖሩ የቅርብ ዘመዶቻቸው እየተረዱ ለመታከም ደፋ ቀና የሚሉ ታካሚዎች እንኳ በቂ ምግብ ሳያገኙ የሚወስዷቸው መድሃኒቶች ከሌሎች መድሃኒቶች፣ ከምግብ፣ ከተደራራቢ በሽታዎች፣ ከተፈጥሮ ባህርይና ወዘተ ጋር በመቃረን ለአካል ጉዳትና ለሞት እየተዳረጉ የሚገኙ ቁጥራቸው በርካታ ለመሆናቸው ዜናዎች ይጠቁማሉ።

በተለያዩ ጉድለቶች የተበከለው የሕክምና ዘርፍ አገልግሎት ሁኔታ፣ የንጹህ ውሃ እጥረት፣ ከግማሽ ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ በድህነት የተጠቁ ዜጎች ለመንገድ አዳሪነት መዳረግ፣ በአውላላ ሁኔታ የሚፈሰው የቆሻሻ እጣቢ ፍሳሽ፣ በነዚህና በሌሎችም ምክንያት የተነሳ ለኮሌራም ሆነ ለሌሎች ተላላፊ በሽታዎች መከሰት ረግረጉ የተመቻቸ መሆኑ የሚታይና የሚታወቅም ነበር። ነገር ግን የኮሌራ በሽታ የሚያስከትለው ጉዳት የታወቀ በመሆኑ ለዚህ ቀልጠፍ ያለ ምርመራና አስቸኳይ እርምጃ በመውሰድ በሽታው እንዳይስፋፋና ብሎም የበለጠ ጉዳት እንዳያደርስ የመከላከል ጥረት በማድረግ ፈንታ የአገዛዙ ቁንጮ የሆነው መለስ ዜናዊ ባለፉት ጊዜያት ረሃብን አስመልክቶ እንደዋሸው ሁሉ አሁንም የኮሌራ በሽታ በመዲናዋ መከሰቱን ለመካድ መሞከሩ ታውቋል። በአሁኑ ወቅት በዚህ የመለስ አገዛዝ ፖሊሲ ምክንያት 14 ሚሊዮን ዜጎቻችን በባዕዳን የምግብ እርዳታ ለመኖር መገደዳቸው ግልጽ ነው። ይህ ሕዝብን ለጥፋትና ለጉዳት የሚዳርግ እርምጃ በጥብቅ መወገዝ ያለበትና እንዳይደገምም ሁሉም ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ሊገነዘበው የሚገባ ጉዳይ በመሆኑ ኢሕአፓ ለዚህ ጥሪውን ያቀርባል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የአገዛዙ ሌላው ከፍተኛ ባለስልጣንና የመዲና ከንቲባ የሕክምና ባለሙያዎችን ስብሰቦ ያለምንም ማስረጃ ለማስፈራራት የወሰደውንም እርምጃ አጥብቀን እየኮነን ቅን ሃሳቢ የሆኑ የሕክምና ባለሙያዎች ይህንን አስጸያፊ እርምጃ በመቋቋም የበሽታው አይነት ምን እንደሆነ በድፍረት ለመግለጽ መሞክራቸው ተገቢ እርምጃ ነውና ከምስጋና ጋር ከጎናቸው የምንቆም መሆናችንን እንገልጻለን፤ ወደፊትም የተቻላቸውን እንዲያደርጉም ጥሪ እናቀርብላቸዋልን።

በተለይም ኢሕአፓ መንግሥታዊ ያልሆኑ አለም አቀፍ ድርጅቶች ይህንን ከወራት ጀምሮ በኢትዮጵያ በየቀኑ በርካታ ሕይወትን እየቀጠፈ ስለሚገኘው በሽታ አስፈላጊ የሆኑትን የመከላከል እርዳታቸውን እንዲለግሱም በዚህ አጋጣሚ ጥሪውን ያስተላልፋል።